

ꙮ42-1ꙮ

# በሰጠን አዕምሮ እንጠቀም

ከሚጠቀሱ፥

- “ዕውቀት ያልተጨመረበት ትጋት ጠቃሚ አይደለም (ምሳሌ 19፥2)
- “ደካማ አዕምሮ አጉልቶ እንደሚያሳይ መነጽር (microscope) ነው፤ ጥቃቅኑንና የማይረባውን ያሳድጋል፤ ትላልቁን ግን መቀበል አይችልም”። (ቸስተር ፊልድ)
- “የጥቂቶች አዕምሮ ሲያረጅ፥ የብዙዎች ግን ይሻግታል”። (ቦሺ)
- “ብልሆች መማርን ይፈልጋሉ፤ ሞኞች ግን በድንቁርናቸው ይረካሉ” (ምሳሌ 15፥14)
- “ስንፍና፥ ሳይደክሙ ማረፍ እንጂ ሌላ ነገር አይደለም”። (ጁለስ ሬናርድ)
- “እውነተኛ መሪ ለመሆን ራዕይ ያስፈልገናል። ያለ ራዕይ ለመምራት መሞከር፣ ያለ ዓላማ ጥሩምባ (እምቢልታ) እንደ መንፋት ይሆናል”። (ቲዮዶር ሽስበርግ)
- “ከጠቢባን ጋር ብትወዳጅ፥ ጠቢብ ትሆናለህ፤ ማስተዋል ከጎደላቸው ሰዎች ጋር ጓደኛ ብትሆን ግን ትጠፋለህ” (ምሳሌ 13፥20)

እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ብዙ አስደናቂ የሆኑ ስጦታዎችን ሰጥቶናል። ከስጦታዎቹ መካከል አንደኛው ጥሩ የሚያስብ አዕምሮ ነው። ጥበብና ዕውቀት ሰው ከእግዚአብሔር የሚሰጠው መሆኑን ብዙ ቦታ መጽሀፍ ቅዱስ ያሳየናል። “ጥበብን ለጠቢባን፣ ዕውቀትንም ለአስተዋዮች የሚሰጥ እርሱ ነው” ይላል (ዳኔል 2፥21)። እንዲሁም ሰለሞን “በዚህ ዓለም የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ጠቢባን መሆን ይገባቸዋል፤ ምክንያቱም ጥበብን ማግኘት ርስትን የመውረስ ያህል ነው” ይላል (መክብብ 7፥11)። በዘመኑ ያለነው አማኞች እግዚአብሔር የሰጠንን መልካም አዕምሮ ምን ያህል እንደምንጠቀምበት ይሆን? እርግጥ ነው እግዚአብሔር የዓለም ጠቢባንን ሊያሳፍር የመረጠው ተራ ሰዎችን ነው። ይሁን እንጂ “ተራ ሰዎች” በእግዚአብሔር እጅ ሲገቡ አዋቂዎችና አስተዋዮች ሊሆኑ እንደሚችሉ መዘንጋት የለብንም። አልፎ አልፎ የምንሰማቸው አስተያየት እግዚአብሔር በሰጠን አዕምሮ መጠቀም መንፈሳዊነት እንደጎደለው ነው። “በእግዚአብሔር መንፈስ እንጂ በሰው ዕውቀትና ጥበብ አልመራም” የሚለው አነጋገር የተለመደ ሆኗል። ጥበብን አልፈልግም” ማለት “የእግዚአብሔርን ስጦታ አልቀበልም” ማለት” ይሆናል። ጥበብ አስፈላጊ ባይሆን ኖሮ “ከእናንተ መካከል ጥበብ የጎደለው ሰው ቢኖር እግዚአብሔርን ይለምን፤ እግዚአብሔርም ይሰጠዋል፤ ምክንያቱም እርሱ ምንም ሳይከለክል ለሁሉም በልግስና የሚሰጥ አምላክ ነው” (ያዕቆብ 1፥5) በማለት እንድንጸልይ ባልተነገረንም ነበር። መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች ጥበበን በመስጠት የማይታየውን፣ የተደበቀውን ምስጢር ይገልጻል። “ዕውቀትን ወይንም ጥበብን አልፈልግም ማለት “መብራት አጥፍቼ ጨለማ ቤት ውስጥ መቀመጥ እፈልጋለሁ” ማለት ይመስላል። ይሄም ሞኝነት ነው።

እግዚአብሔር አሻንጉሊት (Robot) አድርጎ አልሠራንም

እግዚአብሔር በእያንዳንዳችን ሕይወት ብዙ አስደናቂ ስጦታዎች ሰጥቶናል። ይሁን እንጂ አንዳንዶቻችን በባትሪ የሚሠራ አሻንጉሊት (Robot) እንመስላለን። ሲያስቀምጡን የምንቀመጥ፣ ሲያንቀሳቅሱን ብቻ የምንንቀሳቀው፣ ተናገሩ የተባልነውን ብቻ ምንም ሳንጨምር ወይንም ሳንቀንስ የምንናገር ነን። ማንንም ቅር ማሰኘት አንፈልግም። በራሳችን አዕምሮ ሳይሆን በሌሎች አዕምሮ የምናስብ እንመስላለን። ሕይወታችን ወዴት እንዲያመራ ወሳኞቹ ሌሎች እንዲሆኑ የፈቀድንላቸው ይመስላል። ከፈቃዳቸው ውጪ መውጣት ድጋፋቸውን የሚያሳጣን ስለሚመስለን እነርሱን ከደነገጉትና ካወጡት ሕግ አንወጣም። የራሳቸው አቋም የሌላቸው ሰዎች ደካሞች ናቸው። የኑሮ ጓደኛ የምትፈልግ ወጣት የሕይወቱ አቅጣጫ ወዴት እንደሚያዘነብል የሚያውቀውን፣ አደጋ ያለበትም እንኳን ቢሆን ሳይፈራ በድፍረት እምርጃ የሚወስደውን “ምን እያሰበ ይሆን” እያለች የማትጠራጠረውን ወንድ ባል እንዲሆናት ትመርጣለች እንጂ፥ “አንቺ እንዳልሽ ብቻ ይሁን” እያለ የሚኖረውን፣ የራሱ የሆነ መመሪያና ራዕይ የሌለውን ወንድ አትፈልግም።

ዕውቀት ይቀርጸናል

ነገር ጨልሞ የሚታያቸው ሰዎች በቀላሉ ተስፋ የሚቆርጡ፣ የሚበሳጩ፣ የተስፋ ማጣት ስሜት የሚያጠቃቸው

ናቸው። በራሳቸውና እንዲሁም በሌሎች ሰዎች እምነት የላቸውም። የሚያዩት ከፊት ለፊታቸው ያለውን ግልጽ ሆኖ የሚታየውን ብቻ ነው። ነገር ብሩህ ሆኖ የሚታያቸው ሰዎች ግን የሚያዩት ከፊት ለፊታቸው ያለውን ጨለማውንና ጉሙን ብቻ ሳይሆን በአሻገር ራቅ አድርገው የመመልከት ችሎታ ስላላቸው የጠራ ሰማዩን፣ ከዋክብቱን፣ ጸሀዩንና ጨረቃውን ያያሉ። እነዚህ ከላይ የገለጽናቸው ሁለት ዓይነት ሰዎች ሁለቱም ያሉበት ሕይወትና አካባቢ አንድ ዓይነት ቢሆንም አስተያየታቸውና አመለካከታቸው ፍጹም የተለያየ ነው። ያላቸው አመለካከት የሕይወታቸውን ዕድገትና እርምጃ ይወስነዋል።

በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 25 ኢየሱስ ስለ ሦስቱ አገልጋዮች በምሳሌ የተናገረውን ታሪክ እናስታውሳለን። አንድ ሰው አገልጋዮቹን ጠርቶ እንደችሎታቸው ለአንዱ አምስት ሺ ብር፣ ለአንዱ ሁለት ሺ ብር፣ ለአንዱ ደግሞ አንድ ሺ ብር እንዲነግዱበት ሰጥቶ ወደ ሩቅ አገር ሄደ። ከብዙ ጊዜ በኋላ መጣና ከአገልጋዮቹ ጋር ሂሳብ መተሳሰብ ጀመረ። አምስት ሺ ብር የተሰጠው ሌላ አምስት ሺ ብር አተረፈ። ሁለት ሺ ብር የተሰጠው ሌላ ሁለት ሺ ብር አተረፈ። አንድ ሺ ብር የተሰጠው ግን ምንም ሳይተርፍ ዋናውን ይዞ ቀረበ። ለምን እንዳላተረፈ ምክንያቱን ሲገልጽ *"ጌታ ሆይ! ካልዘራህበት የምታጭድ፣ ካልበተንህበት የምትሰበስብ ጨካኝ ሰው መሆንህን አውቃለሁ፤ ስለዚህ ፈራሁና ሄጄ ገንዘብህን በመሬት ውስጥ ቀርበርሁት፤ ይኸውልህ ገንዘብህ አለው"* (ማቴዎስ 25፥24-25)። በተሰጣቸው መክሊት የተጠቀሙበት ጌታቸውን ደስ ያሰኙት ከመሆናቸውም ሌላ፥ ሽልማታቸው ትልቅ ነበር። በመክሊቱ ያልተጠቀመበት ጌታውን ከማሳዘኑም በላይ ፍርዱ ከባድ ሆነ። የተሰጠውን መክሊት እንዴት መጠቀም እንደሚችል ራዕይ ያልነበረው ያ ሰው ሁሉ ነገር ጨልሞ ታየው። በራሱና በጌታው ላይ እምነት አልነበረውም። ሁሉ ነገር አስፈራው። የራሱን ድክመት ወደ ሌላው ማስተላለፍ ጥሩ ምክንያት ይሆነኛል ብሎ ስላሰበ፥ ጌታው የሌለው ባህሪ መስጠት ጀመረ። "…ጨካኝ ሰው መሆንህን አውቃለሁ…" አለ። በራሱ እምነት የሌለው የራሱ የሆነ መመሪያ ወይንም ራዕይ የሌለው ሰው እጁን አጣምሮ መቀመጡ ብቻ ሳይሆን የሚሠሩትን የሚንቀሳቀሱትን መንቀፍ፣ ልዩ መልክና ቅርጽ ማውጣት እንዲሁም ልዩ ልዩ የቅጽል ስም መስጠት ይጀራል። በራሱን ሕይወት መልካም ነገር ማየት የማይችል መሆኑ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ሰዎች ሕይወትም በጎ ነገር አለ ብሎ አይገምትም። ሁልጊዜ ተጠራጠሪና ፈሪ ነው።

ጥበብንና ዕውቀትን መፈለግ ኃጢአት ይሆን?

ሰው በተፈጥሮ "የዕውቀት፣ የጥበብ" ፍላጎትና ጥማት በውስጡ አለ። ይሄም በመጀመሪያዋ ሴት በሔዋን ሕይወት ታይቷል። "ሴቲቱ ዛፉ…ጥበብን የሚያስገኝ እንደሆነ በተመለከተች ጊዜ…" ይላል (ዘፍጥረት 3፥6)። የሔዋን ችግሯ "ጥበብን" መፈለጓ ሳይሆን፥ "ጥበብን" ለማግኘት የሞከረቸው ከመስመር በወጣ መንገድ በመሆኑ ነው። "እግዚአብሔር ለሰለሞን እጅግ አስደናቂ የሆነ ጥበብንና አስተዋይነትን እንዲሁም ወሰን የማይገኝለትን ዕውቀት ሰጠው" (1ኛ ነገሥት 4፥29) ይላል። "ጥበብ" አስፈላጊ ባይሆን የማይጠቅም ቢሆን ኖሮ ለሰለሞን እግዚአብሔር ጥበብን ባልሰጠውም ነበር። ሰለሞንም የጥበብን አስፈላጊነት ተገንዝቦ ባይጠይቅ ኖሮ መቀበል ባልቻለም ነበር። "ምን እንድሰጥህ ትፈልጋለህ?" (2 መጽሐፈ ዜና 1፥7) የሚል ጥያቄ ሲቀርብለት፥ ሰለሞን "ሕብህን በትክክል ለመምራት የሚያስችለኝን ጥበብና ዕውቀት ስጠኝ፤ ይህ ካልሆነ ግን ታላቅ ሕዝብህን እንዴት ልመራ እችላለሁ?" (2 መጽሐፈ ዜና 1፥10) ሲል ጥበብ እንዲሰጠው ጠየቀ። እግዚአብሔርም "…ጥበብና ዕውቀትን መጠየቅህ ትክክል ነው፤ ስለዚህ እነሆ የጠየቅኸውን ጥበብና ዕውቀት እሰጥሃለሁ…" (1፥11-12) አለው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የቀድሞ መንፈሳዊ አባቶች ጥበብንና ዕውቀትን በጣም ከተመኙ፤ በዘመኑ ያለን አማኞች ጥበብና ዕውቀት አያስፈልገንም ለምን እንላለን? "ጥበብና ዕውቀት" ለመንፈሳዊ ዕድገታችንና አገልግሎታችን ይጠቅመናል እንጂ አይጎዳንም። በጥበብ እንራመድ" የሚለውን አማኝ አንዳንድ ክርስትያኖች "የደረቀ ክርስትያን ነው፤ መነፈስ ቅዱስ የለበትም" ይሉታል። ለምን ይሆን?

1) በማስተዋል ሕይወቱን ለመምራት የሚፈልግ ሰው ብዙ ጊዜ "ስሜቱን" ብቻ ተከትሎ የሚሄድ ስላልሆነ፥ በቀላሉ በስሜት ሲከንፍ አይታይም። "ስሜት" የለውም ማለት ሳይሆን ስሜቱን መስመር ማስያዝ ስለሚችል ለሰዎች አይታይም። ሌሎች ስለ አደረጉት ብቻ "እኔም ማደርግ አለብኝ" አይልም። ውጪያዊ የሆነ እንቅስቃሴ እንደ አንዳንዶቹ ባለማሳየቱ "የታሠረ ነው፤ መንፈስ የለበትም" ይባል ይሆናል። ይህን ዓይነት አስተያየት እንዲሰጥበት ካልፈለገ የግድ አካባቢውን መስሎ መገኘት አለበት። ይሁን እንጂ በአዕምሮው የበሰለ ስለሆነ እነርሱን ለመምሰል ብቻ ምንም ነገር አያደርግም።

2) በጥብብና በማስተዋል ሕይወቱን የሚመራ ለአዕምሮው ነጻነት አይከለክልም። በአዕምሮው ውስጥ ጥያቄ ቢፈጠር ያልገባውን ቢጠይቅ "ኃጢአት ነው" ብሎ አያምንም። ሁሉንም "አሜን" ብሎ መቀበል አይሆንለትም። ይህን የሚያዩ አንዳንድ አማኞች "አንተ በአንጎልህ ነው የምትመራው" ሲሉ ወቀሳ ያሰሙታል። "ጥሩ ክርስትያን ነው" ብሎ

የሚያስጠጋው ሰው ስለማይኖር ብቸኛ ይሆናል። የሚያሳዝነው ብቸኛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፥ በውስጡ ያለው ዕውቅትና ጥበብ ይኸውም በማስተማርና በአስተዳደር ሊጠቅም ሲችል ያለ አገልግሎት ተገፍቶ ከዳር መቀመጡ ነው። ቤተ ክርስትያንን በተለያየ የአገልግሎት ዘርፍ ሊጠቅሙ ሲችሉ “በዝምተኛነታቸው” ብቻ ዕውቀታችውና ጥበባቸው የሻገተባቸው ስንት ይሆኑ?

3) በጥበብና በማስተዋል ሕይወቱን የሚመራ የነገሩትን ሁሉ “እሺ እንዳልክ” ብሎ የሚቀበል “ተቀመጥ” ሲሉት የሚቀመጥ “ተናገር” ሲሉት ብቻ የሚናገር፣ “አድርግ” የሚሉትን ብቻ የሚያደርግ፣ “እመን” የሚሉትን ብቻ የሚያምን አይደለም። ይህን ማለት ትህትና የጎደለውና የማይታዘዝ አስቸጋሪ ሰው ነው ማለት አይደለም። ካልገባው የሚጠይቅ፣ ካልተስማማው “አልተስማማኝም” የሚል ነው። የማይጥምና የማይዋጥለት ነገር ሲያጋጥመው እየመረረው ዝም ብሎ የሚውጥ አይደለም። ስለዚህ “ስሜታዊ” ለሆኑት አንዳንድ ሰዎች የእንዲህ ዓይነት ሰው አቋም እንድግዳ ሰሚሆንባቸውና እነርሱን ስለማይመስልብቻ፥ መንፈስ ቅዱስ እንደሌለበት በጥበብና በዕውቀት ብቻ የሚመራ አድርገው ይገምቱታል።

..........................................................................................

**በሚቀጥለው ክፍል እስክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**